# ርዕስ፡ የገጠር ኢትዮጵያ የልማት ሁኔታና ተስፋ

አየነው እጅጉ (የኢትዮጵያ ሣይንስ አካደሚ)

# የንግግር አቀራረብ

1. የገጠር ኢትዮጵያ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሚና
2. የ2012 ዓ.ም. የመንግሥት ባጀት ምድባ በንጽጽር
3. የተለያዩ ጠንካራ አገራት የግብርና ድጎማ
4. ያለፉት ጥቂት ዓመታት የሰብል ልማት አፈጻጸም
5. ከፕሮፌሶር ደሳለኝ ራህማቶ አያሌ የገጠር ጥናቶች የተወሰደ የገጠር መሬት ይዞታ መረጃ
6. የ2012 ዓ.ም. የፌደራል መንግሥት የሰብል ልማት ዕቅድ
7. ስለ ገጠር ኢንዱስትሪ ልማት መጀመር አስፈላጊነት
8. የግብርናና የገጠር ልማት ስለማጠናከር ምክረ-ሀሳብ

1. የገጠር እትዮጵያ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሚና (2010 ዓ.ም.)

| መለኪያ | ከአገሪቱ ያለው ድርሻ (በመቶ) |
|---|---|
| የሕዝብ ብዛት ድርሻ | 85 |
| የሠራተኛ ብዛት ድርሻ | 80 |
| የአገር ዓመታዊ ምርት (GDP) ድርሻ | 35 |
| የግብርና የወጪ ንግድ ድርሻ | 80 |
| የውጭ ምንዛሪ ግኝት ድርሻ | 80 |
| የፌደራል የ 2012 ባጀት የገጠር ልማት ድርሻ | 3.75 |

## 2. ቀጥተኛ የግብርናና የገጠር ልማት የፌደራል ባጀት ድርሻ

ከአገሪቱ ሠራተኛ የገጠሩ ድርሻ 80 በመቶ

ከአገሪቱ የወጪ ንግድ (EXPORT) የገጠሩ ድርሻ 80 በመቶ

በ2001/2 የግብርና የፌደራል ባጀት 9.7 ቢሊዮን ብር

በ2011/12 የግብርናና የገጠር ልማት ባጀት 12.59 ቢሊዮን ብር (ለ80 ሚሊዮን ሕዝብ)

የ2011/12 የግብርናና የገጠር ልማት ባጀት በ2001/2 ብር 4.85 ቢሊዮን ብር

*(ያለፉት 10 ዓመታት አማካይ ግሽበት 10 በመቶ ተብሎ ተወሰዷል።)*

### የ2011/12 የገጠር ልማት ባጀት የ2001/2 ባጀት ግማሽ ነው።

የ2011/12 የከተማ ልማት ባጀት (ለ20 ሚሊዮን ሕዝብ) 56.6 ቢሊዮን ብር

የ2011/12 የትምህርት ባጀት 50.6 ቢሊዮን ብር

የኢኮኖሚ ድርሻ፣ የሕዝብ ብዛትና የባጀት ምደባ አልተጣጣሙም።

## 3. የተለያዩ አገራት ለገጠር ልማትና ለድህ ዜጎች የመደቡት ድጎማ

በሁሉም የለሙና ባልለሙም ብዙ አገሮች ያለ ቢሆንም፣ ለዓይነት ያህል ብቻ፣ የአሜሪካ፣ የአውሮጳና የቻይና የድጎማ ተሞክሮ እንደሚከተለው ነው፡፡

| | |
|---|---|
| **አሜሪካ ከ2011 እስከ 2015** | **867 ቢሊዮን ዶላር** |
| **ቻይና እአአ በ2015** | **248 ቢሊዮን ዶላር** |
| **አውሮጳ ሕብረት እአአ በ2019** | **59 ቢሊዮን ዩሮ** |

የአሜሪካና የአውሮጳ ድጎማ ዓላማው፡- 1ኛ/ ሰፊ ክምችት ይዞ ገበያ ለማረጋጋት፣ 2ኛ/ ትናንሽ አርሶ-አደሮችን ለመርዳትና 3ኛ/ የገጠር ልማትን ለማጠናከር ነው፡፡ ቻይናም እንዲሁ 1ኛ/ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ 2ኛ/የአርሶ-አደሩ መራብ ለአገር ሰላም ጠንቅ እንዳይሆን ለማድረግ፣ 3ኛ/ ለኢኮኖሚ ዕድገት አስፈላጊ መሆኑን በማመን ነው፡፡ በቻይና እአአ ከ1982 ጀምሮ ግብርናው የሚመራው በገዢው ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ ነው፡፡

# 4. የቅርብ ዓመታት የሰብል ልማት አፈጻጸም

## የ2008-2011 የሰብል ልማት ዓላማዎች፡-

- የምግብ ፍጆታን ማሟላትና የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ
- ለፋብሪካዎች ግባት ማምረት
- ለውጭ ገበያ በብቃት ማምረትና የውጭ ምንዛሪ ግኘት ማሳደግ

## በአገዳ፣ ብርዕ፣ ጥራጥሬና በቅባት እህሎች ምርት የግብርና ስኬት

| የምርት ዘመን | ምርት በሚሊዮን ኩንታል | ከዕቅድ የተሳካው(በመቶ) | የምርት ዕድገት (በመቶ) |
|---|---|---|---|
| 2007 | 270.4 | - | - |
| 2008 | 266.8 | 91 | -1.33 |
| 2009 | 290.4 | 91 | 8.84 |
| 2010 | 306.1 | 89 | 5.41 |
| 2011 | 315.6 | 78 | 3.10 |
| **በ2008-2011 አማካይ ዓመታዊ ዕድገት** | | | **3.97** |

- የምርት ዕድገት ደካማ ነበር ፡፡ የአንዳንድ ሰብሎች ምርታማነት ቀንሷል፡፡ የግብርና ልማት ግቦች አልተሳኩም፡፡
- በ2011 ለ 8.3 ሚሊዮን ወገናችን ዕርዳታ ተሰጠ፡፡ የ11.2 ቢሊዮን ብር የውጭ አገር ስንዴ ግዢ ተፈጸመ፡፡

**በ2008-2011 የግብርና ዕድገት ላይ** <u>አስተያየት (2)</u>

- በ2011 ዓ.ም. **የጤፍ የነፍስ-ወከፍ ድርሻ 49.6 ኪሎ፤ የስንዴ (ለዳቦ የሚሆንና የማይሆን) 44.4 ኪሎ፣ <u>የጥራጥሬም 27.5 ኪሎ</u>** ነበር፡፡ ከዚህ የሕዝብ ድርሻ ላይ፣ **ጤፍና ጥራጥሬ** ወደ ውጭም ይላካሉ፡፡

- ጤፍ በቀን ሁለት ጊዜ ቢበላ፣ ከአቅርቦቱ 95 በመቶው ዱቄት ቢሆንና አንዱ ኪሎ ዱቄት 7 እንጀራ ቢሰጥ፣ የአንድ ሰው የቀን ፍላጎት 285.7 [(1000/7) x 2 = 285.7]ግራም የጤፍ ዱቄት ነው፡፡

- በዓመት ለምሣና እራት **104.3** [285.7 x 365/1000 = 104.3] **ኪሎ** ጤፍ ዱቄት **በነፍስ-ወከፍ** ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም፣ የአገር ፍላጎት 113.7 ሚሊዮን ኩንታል ጤፍ ሲሆን፣ የ2011 ዓ.ም. ምርት 54 ሚሊዮን ኩንታል ብቻ ነበር፡፡ **ጤፍ በላተኛው በ109 ሚሊዮን ፈንታ 60 ሚሊዮን ሕዝብ ቢሆን፣ የዓመት የአገር ፍላጎት 63 ሚሊዮን ኩንታል ጤፍ ይሆናል፡፡** ይህም ከዓመቱ 54 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይበልጣል፡፡ በዚያ ላይ ወጪ ንግዱና የቤትና የሆቴል ድግስም ከጤፉ ይካፈላል፡፡

- የዛሬው የዋጋ መናር ካመት ዓመት ብዙ በማይለወጥ የምግብ ምርት ላይ የሕዝብ ዕድገት ታክሎበት፣ **ከፍላጎትና አቅርቦት** አለመጣጣም የመጣ ነው፡፡

# በ2008-2011 የሰው ኃይል ዕድገት ላይ አስተያየት(3)

- በመንግሥት-መር የተማሪ ምደባ ብዙ የዩኒቬርሲቲ ተመራቂዎች ሥራ-አጥ ሲሆኑ፣ ለኤክስቴንሽን አገልግሎት ጥራት ያለው የሰው ኃይል እጥረት እንዳለ በግብርና ሚኒስቴርም ተዘግቧል፡፡ ይህም የ 28 ዓመታት "ተደራሽ" ጥራት-የለሹ የትምህርት ሥርዓት ውጤት ነው፡፡
- ዛሬም፣ 45 የመንግሥት ዩኒቬርሲቲ ባላት አገራችን፣ ከግብርናው እስከ መንግሥት አስተዳደርና ሕክምናው፣ በባቡር ግንባታና አመራር፣ በግድብ ሥራም የሰለጠነ የሰው ኃይል ዕጥረት ይታያል፡፡
- ሥራ-አጥ የሆነውን ባለዲግሪ ወጣት ቁጥር በሙያ፣ በፆታና በዕድሜ ለይቶና ለምን ይህ የዩኒቬርሲቲ ተመራቂ ሥራ-አጥ እንደሆነ ሊመረመርና መፍትሔ ሊፈለግ ይገባል፡፡
- የታወቀ የዘመናት ችግር ወደ ጎን እየተገፋ፣ በያመቱ ባለዲግሪ ሥራ-አጥ በብዛት መፈልፈሉ፣ ከሀብት አባካኝነቱ ሌላ፣ የአገር ዕድገት መሠረትም ያበላሻል፡፡

# በ2008-2011 የግብርና ዕድገት ላይ አስተያየት (4)

- የፌደራል መንግሥት ለከተማ ልማት ለ20 ሚሊዮን ያህል ሕዝባችን 56.6 ብር መድቦ፣ 80 ሚሊዮን ለሚጠጋው  ሕዝባችን የገጠር ልማት ባጀት 12.59 ሚሊዮን ብቻ ነው፡፡ ፍትሐዊ አይደለም፡፡ የ5ቱ ሰብል ልዩ ትኩረቱ መነሻውም ይህ የባጀት ማነስ ሊሆን ይችላል፡፡

- ታሪካዊ የግብርና ዕድገት ባሳየችው ቻይና፣ ግብርና የሚመራው በቀጥታ በገዢው ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ ነው፡፡ ግብርናችንን ለማጠናከር፣ ከባጀት ጭማሪ ሌላ፣ የፌደራል የሚኒስትሮች ም/ቤትና የክልል ም/ቤቶች ቀጥታ ክትትልና አመራር ይጠቅማል፡፡

- ለዘመናት የብዙሀኑ አርሶ-አደር ከሞፈር-ቀንበር አለመላቀቁ፣ የእርሻ መሬት መጣበቡ፣ ሥራ-አጥ መፈጠሩ፣ አርብቶ አደሩ ግጦሽ ፍለጋ መንከራተትና ለዘመናቱ የገጠሩ ድህነት መንገሡ፣ የገጠር አመራር ለውጥ ማስፈለጉን ይጠቁማሉ፡፡

- የገጠር ድህነት (**የ80 ሚሊዮን ሕዝብ**) ቀነሰ/አደገ የሚል ሣይንሣዊ የመንግሥት ጥናትም ባለፉት 28 ዓመታት የለም፡፡ የጥናትም አለመኖር የግብርናውን አመራር ልማዳዊና ውጤት-የለሽ አድርጎታል፡፡

## 4.2 የቤተሰብ የእርሻ መሬት ይዞታ በ2007-2008 ዓ.ም.

| ክልል | አማካይ የቤተሰብ ይዞታ (ሄክታር) | ከ0.5 ሄክታር በታች ያላቸው ቤተሰቦች (ከመቶ) |
|---|---|---|
| ደቡብ | 0.46 | 57 |
| ኦሮሚያ | 1.21 | 25 |
| አማራ | 1.08 | 28 |
| ትግራይ | 0.97 | 36 |
| **ኢትዮጵያ** | **0.95** | **35** |

- **አማካይ የእርሻ መሬት ይዞታ ከአንድ ሄክታር በታች ነው፡፡**
- ከግማሽ ሄክታር በታች ያለው የገጠር ቤተሰብ 35% በመሆኑና በመሬት ኪራይም ከምርቱ እስከ 50% ለመሬት ባለቤት በመከፈሉ፣ ከረሀብ አፋፍ ላይ ያለው የገጠር ወገናችን ቢያንስ 4 ሚሊዮን **(.35 x 12,000,000 = 4,200,000) ነው፡፡**
- መሬት-የለሽና ሥራ-አጥ ወጣቶች **መጠጥ፣ ሌብነትና ሕገ-ወጥነት** እየለመዱ መሆኑ የቅርብ ጥናት ዘግቧል፡፡
- ከምርታማነታችን በጣም ዝቅተኛነት ጋር፣ መሬትም ሰለጠበበ፣ **አማራጭ የገጠር የሥራ ዕድል መፍጠር ለአገር ሰላምና ደህንነት ቅነሳ አስፈላጊ ነው፡፡**
- **በ2011 ዓ.ም.** የምርጥ ዘርና የማዳበሪየ ዕጥረት ነበረ፤ የገበያ ትሥሥር አልነበረም፡፡ ስንዴ በ**11. 1 ቢሊዮን ብር** በ2011 ዓ.ም. ከውጭ አገር ተገዝቷል፡፡

## 5.. **የ2012 የግብርና ዕቅድ**

- የ2012 የሰብል ምርትን መጠን በ21 በመቶ በማሳደግ 382 ሚሊዮን ኩንታል ለማድረስ፡፡
- የ5 ሰብሎችን (**ጤፍ፣ ስንዴ፣ ቦሎቄ፣ ቦቆሎና ሰሊጥ**) በኩታ-ገጠም አሠራር ከ188 ወደ 450 ወረዳዎች ማስፋፋት፡፡
- በ50,000 ሄክታር መሬትና በ4 ቢሊዮን ብር የብድር አቅርቦት፣ **በሥራ-አጥ ወጣቱ ቁጠባ** ላይ ተመርኩዞ፣ ለገጠር ወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠር፡፡
- በ2012  20 የቴክኖሎጂ የልዕቀት ማዕከላት በ50 ሚሊዮን ዩሮ የጀርመን ድጋፍ ገንብቶ የቴክኖሎጂ ሥልጠና መስጠት፡፡
- የቆላ ስንዴ አበረታች ምርታማነትን ተስፋ ወደ ደቡብ፣ አፋርና ሶማሊ ክልሎች ብቻ ማስፋፋት
- ስንዴ በመስኖና ሜካናይዜሽን ማምረቱና ምናልባት ትላልቅ እርሻ ማስፋፋቱም ቀጣይ ናቸው፡፡

## በ2012 የሰብል ግብርና ዕቅድ ላይ አስተያየት (1)

- ባዶ ሰፊ ለም መሬት፣ ብዙ የውሀ ሀብትና አምራች ሕዝብ ያለው አገር፣ የ2012 ዓ.ም. ምርት 382 ሚሊዮን ኩንታል ብቻ እንዲሆን ማቀዱ፣ የምግብ ዋጋን መናር፣ የወጪ ንግድን ውድቀት፣ የውጭ ምንዛሪን ዕጥረት አይገታም፡፡ የዋጋ መናር ችግር ለዜጎችና ለኢኮኖሚውም ጎጂነቱ የታየ አይመስልም፡፡
- ምርታማነት በ2011 ዓ.ም. ለምን እንደቀነሰ የተደረገ ጥናት አልታየም፡፡ ካልተደረገ፣ ማሻሻልም አይታሰብም፡፡
- የቆላ ስንዴ ማስፋፋቱ በ3 ክልሎች ብቻ መወሰኑ ለኢከኖሚው አይረዳም፡፡ **ፍትሐዊም አይደለም**፡፡ ቆላ በሌሎችም ክልሎች እያለ በሶስቱ መከለሉ፣ **በባጀት ማነስ ሊሆን ይችላል፡፡**
- 5 ሰብሎች (**ቦቆሎ፣ ቦሎቄ፣ ስነዴ፣ ጤፍና ሰሊጥ**) ላይ ትኩረት ተደርጎ በ450 ወረዳዎች ብቻ እንዲስፋፉ መወሰኑ የገጠርን ዕድገት ይገድባል፡፡ **እንስትን፣ ጥጥንና የቢራ ገብስን** የመሳሰሉ ወሳኝ ሰብሎች ባለመኖራቸው **ፍትሐዊም አይደለም**፡፡ እንደገና **ችግሩ የባጀት ማነስ ሊሆን ይችላል፡፡**

# በ2012 የሰብልና እንስሳት ግብርና ዕቅድ ላይ አስተያየት(2)

- አርሶ-አደሩና አርብቶ-አደሩ የገበያ ትሥሥር ይደራጅልን እያለ በያመቱ ሲወተውት ጥያቄው በዕቅዱ መልስ አላገኘም፡፡ **እንደገና ችግሩ በከፊል የባጀት ማነስ ሊሆን ይችላል፡፡**

- የምርት ግባት አቅርቦትና ውድነት ችግሮች በያመቱ ቢደጋገሙም በዕቅዱ አስተማማኝ መልስ አይታይም፡፡ **አሁንም ችግሩ በከፊል የባጀት ማነስ ሊሆን ይችላል፡፡**

- የቴክኖሎጂ ማስፋፋት **<u>አለመሳካት ችግር መንስዔው ባለመጠናቱ በዕቅዱ ውስጥ አስተማማኝ መልስ የለም</u>**፡፡ ሥልጠና ብቻውን ብዙሀኑን ድሀ አርሶ-አደርና ድሀ አርብቶ-አደር የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ አያደርግም፡፡

- ምርት 21 በመቶ ለማሳደግ ቢያንስ ቢያንስ በምርት አሰባሰብ ማቀላጠፍና (**ያልተጠበቀ ዝናብ ሲከሰት**) በአዝመራ ጥበቃ (**አንበጣ ለመከላከል**) ላይ **<u>ከባህላዊው አሠራር የተሻለ የፌደራልም ሆነ የክልል ድጋፍ ያለ አይመስልም</u>**፡፡

# በ2012 የሰብል ግብርና ዕቅድ ላይ አስተያየት (3)

- **ሰብል ማብቀል ዓመት ብቻ ቢበቃውም፣** የግብርና ችግሮች **ከዓመት ዓመት አለመወገዳቸው፣** ዛሬም የዓመታት ችግሮችን ተሸክመን ዘመናትን እየገፋን ነው፡፡

- **ጃፓን በ19ኛው ክፍለ ዘመን፣** ከ20 ዓመት ባነሱ ዘመናት፣ የተዋጣለት ዘመናዊ የኢንዱስትሪ መሠረት የገነባችው **ያለምንም FDI፣ ያለምንም ዩኒቬርሲቲ፣ ያለምንም ዘመናዊ ፋብሪካ፣ ያለምንም አገር-በቀል ሊቃውንትና ያለምንም ዘመናዊ መገናኛ፣ በአገር-ወዳድ መሪዎቿና ጀግና ልጆቿ** ያላሰለሰ ትጋትና ብቁ አመራር፣ ከሞላ ጎደል **በሩዝ፣ በሀርና በሻይ** ላይ ብቻ ተመርኩዛ ነበር፡፡

- **ካለን ብርቱ አርሶ-አደር፣ ለም መሬትና ሰፊ የውሀ ሀብት ጋር፣ በመጠኑ ዘመናዊ መገናኛ፣ ብዙ ዘመናዊ ፋብሪካዎች፣ 45 የመንግሥት ዩኒቬርሲቲዎችና አያሌ ምሁራንን ይዘን ራሳችንን መመገብ አልቻልንም፡፡ ለምን አቅመ-ቢስ እንደ ሆንን ጥናት የለም፡፡**

- **የቅርቡ የግብርና ልማት ሥልት የእንስሳት ልማትን ማጠናከር ነው ይባላል፡፡ የሚበጀን፣ አስከፊውን የምግብ ዋጋ መናርና የወጪ ንግድ ውድቀት ለማስተካከል የሰብልና ፍራፍሬ ምርትም አብሮ ተፋጥኖ ማደግ አለበት፡፡**

## 6. የገጠር ኢንዱስትሪ ልማት ስለመጀመር

- ከ4 ሚሊዮን የገጠር ቤተሰብ በላይ ከግማሽ ሄክታር በታች የእርሻ መሬት ያላቸው ናቸው፡፡ መሬት የሌላቸውም ተፈጥረዋል፡፡ መሬት ተከራይተው የሚያርሱትም እስከ ግማሹ ምርት ለባለመሬቱ ይሰጣሉ፡፡ መሬት እየጠበበና የገጠር ሥራ-አጥ ብዛትም እየተባባሰ የሚሄድ ነው፡፡

- በገጠር ኢንዱስትሪ ልማትም ከአፍሪቃም ኋላ-ቀር ነን፡፡ የመሬት መጣበብን ችግር ለመቋቋም፣ የገጠርን ሥራ-አጥ ወጣት ከጥፋት ለማዳን፣ የገጠርን ድህነት ለመቀነስና ሰላም ለማረጋገጥ የገጠር የኢንዱስትሪ ልማት ማፋጠን ያስፈልጋል፡፡

- መነሻ ሊሆኑ የሚችሉ የገጠር የልማት ተቋማት የሚከተሉትን ሊጨምር ይችላል፡-

  - የግብርና ግባቶች መደብር፣ የምርትና የሸቀጣ-ሸቀጥ መደብር፣ **የዱቄት፣በርበሬና ሽሮ ወፍጮ**
  - **የምግብ ዘይት ፋብሪካ፣** የፍራፍሬ ፋብሪካ ፣የጥጥ መፈልቀቂያ ፈብሪካ
  - የፋብሪካና የግብርና መሣሪያዎች ጥገና ማዕከል፣ የባህል ዕደ ጥበባት ድጋፍ ማዕከል
  - የደንና የውሀ ውጤታማ አጠቃቀምና ልማት
  - የአናጢና የብረታ ብረት ሥራ ማዕከል (**ለምሣሌ፡-የሰውና የዕቃ ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ለመሥራት**)

- **ልማቱ በግብርና ኤክስቴንሽን 12,500 የአርሶ-አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ውስጥ ሊከናወን ይችላል፡፡**

- **ስለ አፈጻጸሙ በጥናት ወረቀቱ ውስጥ ዝርዝር አስተያየት ተሰጥቷል፡፡**

## 7. የግብርናና የገጠር ልማት ማጠቃለያ ምክረ-ሃሳብ

- ❖ የገጠርን አስፈሪ የመሬት መጣበብና አደገኛ የሥራ-አጥ/ቦዘኔ አዝማሚያ ለመቋቋም፣
- ❖ የአገሪቱን አብዛኛውን ሕዝብ (80 በመቶ አካባቢ) ባግባቡ ያላካተተ ልማት የአገርን የልማት ፍላጎት ሊያሟላ ስለማይችል፣
- ❖ ግብርናውን በማሳደግና የኢንዱስትሪንና የአገልግሎት ዘርፉን ሽግግር በማፋጠን ለሥራ-አጡ አርሶ-አደርና ወጣት የሥራ ዕድል በመክፈት፣ የገጠርን ሰላም አስተማማኝ ለማድረግ፣
- ❖ ባለፉት ዘመናት አካሄዳችን የኢኮኖሚው ችግርና የገጠሩ ድህነት እየተባባሱ ስለመጡ፣

ከሕዝባችን 80 በመቶውን የገጠር ወገናችንን የዘመናት ኋላ-ቀርነትና የዋጋ መናር ችግር ለመለወጥና የብዙሀኑ ኢትዮጵያውያንን የገጠር ልማት፣ እንዲያም ሲል የሙሉ ኢትዮጵያን ልማት፣ ለማፋጠን የሚከተለው ምክረ-ሃሳብ ቀርቧል፡-

## ማጠቃለያ (1)፡-

1ኛ/ የግብርናና የገጠር ልማት ባጀት ከሕዝቡ ብዛትና ከኢኮኖሚ ጋሻነቱ ጋር ቢመጣጠን ይሻላል፡፡ በ2012 ዓ.ም. 20 ሚሊዮን አካባቢ ለሆነው የከተማ ሕዝብ ልማት የፌደራል ባጀት 56.6 ቢሊዮን ብር ሲሆን፣ ለ80 ሚሊዮን ያህል ሕዝብ የገጠር ልማት የተመደበው 12.59 ቢሊዮን ብር ብቻ ነው፡፡ ገጠሩ በብቃት ሳያመርትና ራሱም እየተራበ፣ የዋጋ መናር ቅነሳ፣ የውጭ ምንዛሪ ዕድገትና የከተማ ልማትም ሊሳኩ አይችሉም፡፡ ከአገር ፍላጎት ተርፎ፣ ለወጪ ንግድ የሚሆን ሰፊ የምርት ክምችት ሳይኖር፣ ወጪ ንግድን ለማጠናከር በሚል ሰበብ፣ የብሩን የመግዛት አቅም መቀነሱ፣ ወጪ ንግድ ሳያድግ የገቢ ንግድን ዋጋ ስለሚያንር፣ የወቅቱን የዋጋ መናር እሮሮ ማባባስ ነው፡፡

2ኛ/ የግብርናን ምርምርና የግብርና ኤክስቴንሽንን ቅንጅት ይበልጥ በማጠናከር፣ የምርምርም ቅደም-ተከተል በማውጣት *(ለምሣሌ የሎሚ በሽታ ምርምር ከእንሰት በሽታ ምርምር መቅደም የለበትም)*፣ ዛሬ ላይ የለሙ አገሮችን ሲሶ አካባቢ የሆነውን ምርታማነት አፋጥኖ በማሳደግ፣ ከሸማቾችም ጋር ሕጋዊ የገበያ ትሥሥር በማደራጀት፣ የክልል ም/ቤትና የሚኒስትሮች ም/ቤት አፈጻጸሙን በቀጥታ ቢቆጣጠሩት ፈጣንና አርኪ ውጤት ሊገኝ ይችላል፡፡

3ኛ/ የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ የቻይናን ግብርና በቀጥታ በመቆጣጠር በገጠር ድህነት ቅነሳ ላይ በዓለም የተደነቀ ውጤት አሳይቷል፡፡ አስከፊ የዘመናት ድህነትን ለመዋጋትና የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ያለፉት 29 ዓመታት የግብርና ሚኒስቴር አመራር ስላልተሳካለትና ያንኑ ያልተሳካለትን አመራር ይዞን ከመራብ፣ አመራሩን በቀጥታ በሚኒስትሮች ም/ቤትና በክልል ም/ቤቶች ሥር ማድረጉ ለሕልውናችንና ለአገር ሰላምም አስፈላጊ ለውጥ ነው፡፡

## ማጠቃለያ (2)፡-

4ኛ/ ከ0.5 ሄክታር በታች የእርሻ መሬት ላላቸው አርሶ-አደሮችና ለሥራ-አጥ ወጣቶች የገጠር ልማት ተቋማት በመክፈት ቋሚና አዳጊ የኑሮ መሠረት የሚሆን የገጠር ኢንዱስትሪ ጅማሮ በመንግሥት ድጎማና ብድር ቢገነባ ይሻላል፡፡

5ኛ/ ብዙ ሥራ-አጦች ካሏቸው ከተሞችና አካባቢያቸው *(ለምሣሌ አዲስ አበባ፣ አዳማ፣ ባህር ዳር፣ ድሬዳዋ፣ ሐረር)* የዶሮ ርቢ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ እርሻዎች ቢደራጁ፣ ሥራ-አጥ ወጣት አምራቾች ኢኮኖሚውን ደጉመው፣ ሸማቾችንም ጠቅመው ራሳቸውም ከሰፊው የከተማ ገበያ ይጠቀማሉ፡፡

6ኛ/ ኮምባይንን መንግሥት፣ የግል ኩባንያዎችና አምራች ማህበራት ቢገዙና በከፍተኛ ድጎማ ቢያከራዩ ይጠቅማል፡፡ ዛሬ ላይ ምንም ዓይነት የኮምባይን ሥልጠና ለድሀ አርሶ-አደር ቢሰጠውም ያለድጎማ ምንም መሣሪያ ሊገዛ ወይም ሊከራይ አይችልም፡፡ እስኪጠናከር ድረስ የሚሻለው ለጊዜው በድጎማ እየተረዳ፣ የግብርና መሣሪያ ፋብሪካ ከፍቶ ለጎጆ ኢንዱስትሪና ለትናንሽ አርሶ-አደር የሚመጥኑ የግብርና መሣሪያዎችና ማጓጓዣዎች መፈብረክና በድጎማ መሸጥ ነው፡፡ በተመሳሳይ መንገድ አገር-በቀል ማዳበሪያም ከአርሶ-አደሩ ጋር በመመካከር ሊዘጋጅ ይችላል፡፡ ሁልጊዜ የውጭ ምርት ጥገኛነት አያዋጣንም፡፡

7ኛ/ የትምህርት ጥራት ለሣይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገት ቅድመ-ሁኔታና ለአገር ሕልውናም ወሳኝ ግባት በመሆኑ የትምህርት ፖሊሲው እንደገና ሊመረመር ይገባል፡፡ ያለ በቂ ሀብትና አቅም በተደራሽነት መርህ ብቻ ባዶ ሰርቲፊኬት በየመንደሩ መታደሉ ባለሰርቲፊኬቱንና ቤተሰቡን ብቻ ሳይሆን የአገርን ዘላቂ ሕልውናም የሚጎዳ ነው፡፡

በትዕግሥት ስላዳመጣችሁኝ  አመሰግናለሁ፡፡